Idol or Tabot.doc -- Program # 18

# *ወይ ጣዖቱን ወይ ታቦቱን*

**ጌታቸው ኃይሌ**

*ለዛሬው ድርሰቴ "ወይ ጣዖቱን ወይ ታቦቱን" የሚል ርእስ እንድሰጠው ያሳሰበኝ፥ የትግራይ ሕዝብ ነፃ አውጪ ግምባር ከመድረክ አባላት ጋር ሲከራከር፥ ግምባሩ ስልጣን ከያዘ ጀምሮ ለኢትዮጵያ ሕዝብ የሠራውን ውለታ ወኪላቸው ሲዘረዝር መስማቴ ነው። የክርክሩ ፍሬ ነገር፥ "የትግራይ ሕዝብ ነፃ አውጪ ግምባር ዲሞክራሳዊ የጭቆና አገዛዝ ካለፉት የጭቆና አገዛዞች መቶ በመቶ የተሻለ ነው" የሚል ነበር። ዲሞክራቶቹ የሚሉት፥ "ከዝንጀሮ ቆንጆ ምን ይመራርጡ፤ የትግራይ ሕዝብ ነፃ አውጪ ግምባር አገዛዝ እንዳለፉት አገዛዞች መቶ በመቶ የፈላጭ ቆራጭና የጭቆና አገዛዝ ነው፤ የዲሞክራሲ መንፈስ በአጠገቡም ሺው አላለ። ከዲሞክራሲና ከጨቋኝነት አንዱን ይያዝ (ወይ ጣዖቱን ወይ ታቦቱን ሁን) እንጂ ዲሞክራሳዊ የጭቆና አገዛዝ የሚባል ፍልስፍና የለም" ነው።*

*በዲሞክራቶቹና በግምባሩ መካከል የማይታረቅ መሠረታዊ የአስተሳሰብ ልዩነት አለ። ግምባሩ የሚለው፥ "ጨቋኝ ገዢን ዲሞክራት የሚያሰኘው ጥሩ ሥራ ሊሠራ ይችላል" ሲሆን፥ ዲሞክራቶቹ የሚሉት፥ "ጨቋኝ ምን ጊዜም ጨቋኝ ስለሆነ፥ በጎ ሥራ ሊሠራ አይችልም፤ ተሳስቶ በጎ ሥራ ቢሠራም፥ በስልጣን ላይ የሚያስቀይ መብት አይሰጠውም፤ መወገድ አለበት። የኢትዮጵያ ሕዝብ የጨቋኝ ባለውለታ መሆን አይፈልግም" ነው።*

*የወያኔዎቹ ተከራካሪዎችን ላዳመጣቸው የሚከራከሩት ከተቃዋሚ ቡድኖች ጋር ሳይሆን ከንጉሡ ነገሥቱና ከደርግ ጋር ነበር። ማለት፥ ወያኔዎች አገዛዛቸውን የሚያስተያዩት ከእነሱ በፊት ከነበሩትና ከተረሱት አገዛዞች ጋር ነበር። "እኛ እነደርግ ያልሠሩትን ይኸን ይኸን ሠርተናል፤ እናንተ ምን ሠራችሁና ነው ከእኛ ጋር የምትወዳደሩት?" እያሉ ስልጣን ይዘው ያልተሞከሩትን ፓርቲዎች ይጠይቋቸዋል። "በእኛ አገዛዝ ሕዝብ በፈለገ ጊዜ ጭቆናችንን ሸሽቶ ቢሄድ አንከለክለውም" ይሏቸዋል። የሚከራከሩት ከደርግ ጋር ቢሆን ኖሮ፥ መልሳቸውን ከደርግ ያገኙት ነበር። ከተቃዋሚዎቹ ጋር ከሆነ ግን፥ መጠየቅ ያለባቸው፥ "ተቃዋሚዎቹ ስልጣን ቢይዙ ምን ያደርጉ ነበር?" ብለው ነበር። ወያኔዎቹ መልሱን ሊገምቱ አይችሉም። ተቃዋሚዎቹ ግን ያማረ፥ የጠራ መልስ አላቸው። እንዲህ ይላሉ፤ "በዲሞክራቶቹ ግዛት ሕዝቡ ከእናት አገሩ ጋር ተቃቅፎ ይኖራል፤ የደርግንና የወያኔን ጭቆና ሸሽቶ የሄደውም በጥድፊያ ይመለሳል እንጂ፥ ዲሞክራሲ ከሰፈነባት ቢመኟት የማትገኝ ኢትዮጵያን ማን ጥሎ፥ ምንስ ፈልጎ ይሰደዳል?"*

*ተቃዋሚዎቹን፥ "እኛ መግዛት እንችላለን፤ እናንተ ግን አትችሉም" ይሏቸዋል። እዚህ ላይ እውነታቸውን ነው፤ ተቃዋሚው የሚያቋቁመው መንግሥት ሕዝብ የሚያስተዳድር፥ ለሕዝብ የሚገዛ፥ ለሕዝብ የሚታዘዝ እንጂ፥ ሕዝብ የሚገዛ፥ ሕዝብ የሚያዝ አይሆንም።*

*የዲሞክራቶቹ አቋም አዲስ አይደለም። የዲሞክራሲን አስተዳደር ለኢትዮጵያ ሕዝብ ለማስገኘት ነው ትግላቸውን ንጉሣዊ አገዛዙን በመቃወም የጀመሩት፤ ከዚያም ደማቸውን እያፈሰሱ፥ የወታደራዊውንና የወያኔን አገዛዝ ወደመቃወም የተሻገሩት። ወያኔዎቹ የዲሞክራቱ አቋም አምሯቸው ከሆነ፥ እውነትም የሚያምር፥ የሚያጎመዥ ነው፤ አይፈረድባቸውም። በሕዝብ ዘንድ በጠላትነት ከመታየት ወደ መወደድ መሸጋገር ነው። ግን ዲሞክራት የሚኮነው ዲሞክራት በመሆን ነው እንጂ፥ የዲሞክራቶቹን ቃላት እየተሻሙ በመለፍለፍ አይደለም። በወያኔ ቤተ መቅደስ ያለው ርእዮተ ዓለም ጣዖት ብቻ እንጂ*

ጣዖትም ታቦትም (አንድም ሁለትም) አይደለም፡፡ ጣዖት ደግሞ ምንም የሐር ግምጃ ቢያለብሱት፥ ምንም የወርቅ ድባብ ቢያጠሉለት ጣዖትነቱን ትቶ ታቦት አይሆንም፡፡

የዲሞክራሲ ክርክር የሚካሄደው በዲሞክራሲ አገዛዝ በሚያምኑና ሁሉም እኩል ጥበቃ በአላቸው መካከል ብቻ ነው፡፡ በክርክርና በውድድር ጊዜ ኢሕአዴግ የሚቀርበው ከፓርቲዎቹ እንደ አንዱ ሆኖ እንጂ መንግሥት ሆኖ አይደለም፡፡ ክርክርና ውድድር እንደ ጦርነት ናቸው፤ የመንግሥት የጦር ኀይልና ጥበቃን መቶ በመቶ በእጁ በያዘ ፓርቲና ምንም ጥበቃ በሌላቸው ፓርቲዎች መካከል በየትም አገር የዲሞክራሲ ክርክርና ውድድር ሲደረግ አላየንም፡፡ መገናኛ ብዙኃን፥ በተለየም ዲዮና ቴሌቪዥን፥ በእጁ በያዘ ፓርቲና በሌሎች ፓርቲዎች መካከል በየትም አገር የዲሞክራሲ ክርክርና ውድድር ሲደረግ አልሰማንም፡፡ ኢሕአዴግ መንግሥቱም፥ መገናኛ ብዙኃኑም፥ ዳኞቹም፥ ሁሉ በእጁ ሁሉ በደጁ ከሆነ፥ ክርክሩ ይህን ከማሳየት አልፎ መካሄድም አልነበረበትም፡፡ አለዚያ አንድ ወጠጤ ጎረምሳ በጠመንጃ አፈ ሙዝ የጠለፋትን ሴት ወይዘሮ ሲያገባ የገዛ ዘመዶቿ ሚዜና እድምተኛ መሆን ነው፡፡ ወያኔዎች ይኸም አልበቃ ብሏቸው ክርክሩ ለሕዝብ ከመሰማቱ በፊት፥ “ጥፋታችንን የሚያጋልጠውን እንሰርዛለን” የሚል ፈሊጥ አመጡ፡፡ የምርጫ ሥነ ምግባሩን ተከራክሮ ያሳወጀው የመላ ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት (መኢአድ) ምክንያቱን በመግለጫ አውጥቶ በውይይቱ ባለመሳተፉ ማንንም ሊገርርመው አይገባም፡፡ ከዚያም አልፎ በምርጫው መሳተፉን ሊሰርዝ እንደሚችል የድርጅቱ መሪ አቶ ኃይሉ ሻውል አመልክቷል፡፡ ሰው እስኪታዘበው ድረስ አምኗቸው ነበር፤ ከዱት፡፡ የወዳጃቸው የፕዚዴንት ካርተር ማእከል ሳይቀር ምርጫውን እንዲመለከት ቢጋብዙት ወጊዱ ብሏቸዋል፡፡ ማእከሉ ስለ 97ቱ ምርጫ በሰጠው መግለጫ ራሱን ሲወቅስ ስለተሰማ፥ የዛሬውን ግብዣ ያልተቀበለው፥ “ካሁን በፊት የዋሸንላችሁ ቆጭቶናል” ማለቱ መኖኑን መገመት ይቻላል፡፡ ሌሎቹም ገና በማወላወል ላይ ናቸው፡፡

ክርክሩን ሳይ፥ ልክ ምጥማጥ ይዞ፥ “የያዝኩት በግ ነው” ከሚል ሰው ጋር የሚካሄድ ክርክር መሰለኝ፡፡ ተከራካሪዎቹ በምጥማጥና በበግ መካከል ያለውን ልዩነት ተራ በተራ ቢነግሩትም፥ መጽሐፍ እየጠቀሱ ሊረቱት ቢሞክሩም አልተቀበላቸውም፡፡ “እምቢ፥ አልረታም” አለ፡፡ “የያዝኩት በግ ነው” ከሚለው አቋሙ ስንዝር አልተነቃነቀም፡፡ ባይሆን እንኳን ምነው “ድመት ነው” ባለ! ቀድሞውንስ መቼ አጣውና ነው የነሱን ገለጻ ያስፈለገው? እንግዲህ ተቃዋሚዎቹ ለመርታት ያላቸው ተስፋ ባለምጥማጡ የሾማቸው ዳኞች በሚሰጡት ውሳኔ ላይ ሊሆን ነው፡፡

የትግራይ ሕዝብ ነፃ አውጪ ግምባር አባላት ዲሞክራት አይደሉም እንጂ፥ ቢሆኑኖሮ፥ መጀመሪያ ሊያደርጉ የሚገባቸው ዳኝነቱን ለቅቀው ገለልተኛ መሆን ነበር፡፡ ባህሉንና ሥርዓቱን ለመማር ደግሞ፥ ቦሩ ሜዳ እያለላቸው ባሕር ማዶ መሻገር አያስፈልጋቸውም፡፡ በአፄ ዮሐንስ ዘመን ካህናቱ በሦስት ልደትና በሁለት ልደት እምነት ተከፍለው እንደነበረ ይታወሳል፡፡ እውነተኛውን ሃይማኖት ለማወቅ ክርክሩን ቦሩ ሜዳ ላይ ሲያደርጉ፥ ዳኞቹ አፄ ዮሐንስ፥ ንጉሥ ምኒልክ፥ እጨጌ ቴዎፍሎስ ነበሩ፡፡ በሁለት ልደት የሚያምኑት እጨጌ ቴዎፍሎስ የሦስት ልደት አማኞች እያየሉ፥ የሁለት ልደት አማኞች እየደከሙ ሲሄዱ ሲያዩ፥ ዳኛ ሆነው ማዳላት ወንጀልም ኃጢአትም ስለሆነባቸው፥ ተቸገሩ፡፡ ድሉን ላለማጣት ሲሉ፥ የዳኝነቱን ወምበር ለቅቀው፥ እንደባለጉዳዮቹ አደግድገው ቆመው ተከራከሩ፡፡ ዳኛም ባለጉዳይም መሆንን ባህላችን አይደግፈውም፡፡

እንዳላሰለቻችሁ ተስፋ እያደረግሁ፥ ክርክሩና የአንዳንድ ሰዎች መታለል ስለ አቶ ጋረደው የሚነገር አንድ አጭር ተረት ላውጋችሁ፡፡ አቶ ጋረደው ከመንደሩ ወጥቶ አያውቅም፡፡ መንደሩ ከአያት ቅድም አያቶቹ አስቀድሞ የነበሩ ዘመዶቹና መንደርተኞቹ የቆፈሩት ጉድጓድ አለው፡፡ አቶ ጋረደውና ሌሎቹ የዛሬዎቹ መንደርተኞች ለራሳቸውና ለከብቶቻቸው ውሐ የሚቀዱት ከዚያ ጉድጓድ በዶጮና በገመድ እየሳቡ ነው፡፡ ሰውየው ከመንደሩ ርቆ ሄደ

ቢባል፥ ከአንድ ጊዜ በቀር፥ ከቤቱ አንድ ሰዓት ተኩል ያህል ከሚያስኬደው በሳምንት አንድ ቀን ከሚውለው የኀሙስ ገበያ ድረስ ነው።

አቶ ጋረደው ከኀሙስ ገበያ ራቅ ብሎ የሄደው የአውራጃው ፍርድ ቤት ለምስክርነት ጠርቶት፥ ከፍርድ ቤቱ ድረስ መሄድ የነበረበት ጊዜ ነው። በዚያ ቀን ከሰዎች ጋር አብሮ ሲሄድ መንገድ ላይ ከትንሽ ምንጭ እየወጣ እንደወንዝ የሚወርድ ውሐ ሲያገኙ፥ እዚያው ከአንድ ዛፍ ጥላ ስር ተቀምጠው፥ የስንቅ ጭብጧቸውን በልተው ከወንዟ ሲጠጡ፥ የወንዝ ውሐ በራሱ ዐውቆ ሲወርድ በማየቱ በጣም ተደነቀ። “ታያላችሁ ይኸን ጉድ? ውሐ እንዴት እንዲህ ዐውቆ ይወርዳል? ምነው ለኛም እግዜር እንዲህ ያለ ወንዝ ቢያፈልቅልንና ውሐ ከጉድጓድ ከመጎተት ቢያድነን” ብሎ ተመኘ።

ከመንገደኞቹ አንዱ የኔታ አያሌው የሚባሉ ደብተራ ነበሩ። የኔታ አያሌው የሰፈሩ የገጠር ቤተ ክርስቲያን ደብተራና የመንደሩ ሕፃናት አስተማሪ ነበሩ። መምህሩ ዕውቀታቸውን የገበዩት ከአንድ አውራጃ ወደሌላው እየዞሩ የታወቁ መምህራን ሊቃውንት ደቀ መዝሙር በመሆን ነበር። በዙረታቸው ጊዜ ዓባይን ካንዴም ሁለቴ ተሻግረውታል። እንዳጋጣሚ አንዴ የሚካኤል ዕለት፥ ሌላ ጊዜ የማርያም ዕለት ስለነበረ፥ ታሪኩን ሲናገሩ የሚካኤል ዕለት አዞ ሊበላቸው፥ የማርያም ዕለት ደግሞ የውሐ ሙላት ሊወስዳቸው ሲል፥ ቅዱስ ሚካኤል ከአዞው፥ ወላዲተ አምላክ ከውሐ ሙላት እንዳተረፏቸው እያስታወሱ ነው። ጎጃም ቅኔ ሲማሩ ከተማሪ ቤቱ ልጆች ብዙዎቹን ተስቦ ገብቶ ሲፈጃቸው አብሮ አደግ ጓደኞቻቸውን ስለወሰደባቸው፥ ሁል ጊዜ ሐዘንተኛ ናቸው። መምህሩ እዚህ መንደር የመጡት ትምህርታቸውን ከጨረሱ በኋላ ያገለግሉበት የነበረው ደብር ካህናት የሚያሳዩት ክርስቲያናዊ ያልሆነ መሠርይነት አሳዝኗቸው ጥለው ሲሄዱ እግር ጥሏቸው ነው።

የኔታ አያሌው በዚያን ዕለት ከመንደርተኞቹ ጋር መንገደኛ የሆኑት ክርክር የተነሣበትን ጉዳይ በሽምግልና ያዋዋሉትና የመዘገቡት እሳቸው ስለነበሩ ነው። ምሳቸውን ሲበሉ፥ ያ ከመንደር ወጥቶ የማያውቅ አቶ ጋረደው ወንዚቷን ሲያደንቅ መምህር አያሌው ሰምተው፥ በተራቸው፥ “ጉድ እኮ ነው፤ ዓባይን ያላየ ምንጭ ያመሰግናል” ብለው ተደነቁ ይባላል።

የትግራይ ሕዝብ ነፃ አውጪ ግምባር የጭቆና አገዛዝ መንገድ ሲያወጣ፥ በየከተማዎቹ ፎቅ ቤት ሲሠራ፥ ክልል ብሎ በሚጠራቸው አውራጃዎች ሁሉ ከአንድ ሀብታም ቤት ብዙ የማይሻለውን ሕንፃ “ዩኒቨርስቲ” ሲለው ያዩና የሰሙ አንዳንድ ሰዎችም፥ ልክ እሱ የሚናገረውን ቋንቋ እየደገሙ፥ አገዛዙን ከንጉሣዊው ቤተሰብና ከደርግ አገዛዝ ጋር እያነጻጸሩ ሲያደንቁ ይሰማሉ። ብራቮ ወያኔ! በእርግጥም፥ ዓባይን ሳያይ ምንጭ የሚያመሰግን አግኝተሃል። በእርግጥም የዲሞክራሲን ኑሮ ያላየ፥ የትግራይ ሕዝብ ነፃ አውጪ ግምባር በገዛበት ዘመን የተሠሩ ሥራዎችን ሊያደንቅ ይችላል።

ንጉሣዊው አገዛዝ ከወደቀ አርባ ዓመት ሊጠጋው ነው። በዛሬው በሃያኛውና በሃያ አንደኛው ምእት ዓመት ዘመን፥ እነዚህ ወደ አርባ የተጠጉ ዓመታት ተአምራት ሊሠራባቸው የሚቻልባቸው ዘመን እንጂ የይስሙላ ዩኒቨርሲቲ የሚቋቋምበት፥ የሕዝቡ የገቢ ምንጭ ሳይሻሻል፥ ሕንፃ የሚሠራበት፥ መንገድ የሚቀደድበት ዘመን አልነበረም። ማንኛው ነው የሚቀድመው? ሕዝቡን መኪና ለመግዛት ማስቻል? ወይስ የሚበላው አጥቶ በረኀብ ለሚያልቀው ሕዝብ የመኪና መንገድ ማውጣት? ዛሬ አዲስ አበባ የሰማይ ቤትና የምድር ቤት መሆኗን በገለልተኝነት አይቶ የሚመሰክርላት ሆናለች። የምድሮቹ ኢትዮጵያውያን ይራባሉ፤ ፎቁን የያዙት ትግራውያንና አጃቢዎቻቸው ጮማ እየቈረጡ ይሳከራሉ።

የትግራይ ነፃ አውጪ ግምባር በአሠራቸው መንገዶች ላይ ታላላቅ የእቃ ማመላለሻ መኪናዎች ይመላለሱባቸዋል። ግን መኪናዎቹ የማን ንብረቶች እንደሆኑና የማንን የንግድ እቃ እንደሚያመላልሱ የማያውቅ ይኖር ይሆን? የሚጣደፉት ሳዑዲ ዓረቢያ፥ ህንድ፥ ፓኪስታን ከገዙት መሬት ላይ የሚያመርቱትን ሰብል ለማጋጋዝ አይደለም። እሱ ቀጥሎ

የሚመጣ ነው:: አሁን የሚያገለግሉት ኢትዮጵያን የግል ኩባንያቸው አድርገው የሚበዘብዟትን የትግራይ ነፃ አውጪ ግምባር አባላትንና ግምባራቸው እንዳይደፋ ደጀን የሆኑ ደጋፊዎቻቸውን ነው::

ዛሬ በሀገሪቱ ውስጥ አሉ የተባሉ የንግድና ሌሎችም የገቢ ምንጮች የተያዙት በትግራይ ሕዝብ ነፃ አውጪ ግምባር አባላት እጅ ነው:: አንዳንድ ሥራዎች በሌሎች ሰዎች የተያዙት በሁለት ምክንያት ነው፤ አንደኛ፥ የትግሬ ወያኔዎቹ ሁሉንም ለመያዝ በቂ የሰለጠነ ሰው የላቸውም:: ሁለተኛ፥ ሕዝቡ በጥቃቅን ሥራ ላይ ደፋ ቀና ሲል፥ በእነሱ ለማግረርና መብቱን ለማስመለስ ጊዜ እንዳይኖረው ታቅዶ የተደረገ ነው:: በቂ የሰለጠነ ደጋፊ የሰው ኀይል ለማፍራት ተግተው የተነሡበትን ሥራ ልብ ብንለው የሚያስደንቅ ሆኖ እናገኘዋለን:: ለምሳሌ፥ ደጋፊ የሚመለምሉበትና መሠረታቸው ያደረጉት የትግራይ ሕዝብ ልጆች የሚቀርብላቸው የትምህርት አገልግሎት ማንም የማይደርስበት ሆኗል። ከኢትዮጵያ መንግሥትም ሆነ ከሌሎች አገሮች ለኢትዮጵያ ተማሪዎች እንዲሆን የተመደበውን ስኮላርሽፕ የሚያከፋፍሉት ይደግፉናል ብለው ለሚገምቷቸው ለትግራይ ልጆች ነው::

በዚህ አጋጣሚ አንድ የሰማሁትን የሚያስገርም ታሪክ ልናገር፤ አንድ ጊዜ ዓሥራ ሁለት የሚሆኑ ኢትዮጵያውያን የኢትዮጵያ መንግሥት ስኮላርሽፕ ተሰጥቷቸው አንድ የውጪ ሀገር ዩኒቨርስቲ ማመልከቻ ያቀርባሉ:: ዩኒቨርስቲው ገንዘብ ይዘው ከመጡ ብሎ ይቀበላቸዋል:: አሁን እንግዲህ ሬጅስትራሩ ወንዶችን በወንዶች መኝታ ክፍል (ዶርም)፥ ሴቶቹን በሴቶች መኝታ ክፍል ለመደልደል ቢፈልግ የኢትዮጵያውያንን ስም ስለማያውቅ ሴቶቹንና ወንዶቹን በስማቸው ጭምር ለመለየት ተቸገረ:: መቼም ዛሬ ኢትዮጵያውያን መምህራን፥ ሐኪሞች፥ ሳይንቲስቶች የሌሉበት አገር ስለሌለ፥ አጠገባቸው ያለውን አንዱን ኢትዮጵያዊ የሕክምና መምህር ጠርቶ፥ ወንዶቹን ከሴቶቹ በስማቸው እንዲያረጋግጥለት እርዳታ ይጠይቀዋል። ተጠያቂው የስሙን ዝርዝር አይቶ፥ “እንዴት በዝርዝሩ ውስጥ ለማላ ያህል አንድ እንኳ ትግሪኛ ያልሆነ ስም የለም!” ብሎ ራሱን ይዞ ጮኸ:: ሰዉ ያየውን እንዳይናገር ምክንያት ስለሚኖረው ነው እንጂ፥ ሌሎች እንዲህ ያሉ ታሪኮች ሞልተዋል::

እንዲህ ከሆነ፥ ራስ የሚያስችል ሥራ የያዙ ሌሎች ኢትዮጵያውያን በሥራ ላይ የሚቆዩባቸው ቀናት የተቈጠሩ፥ የተመጠኑ ናቸው:: እስከዚያ ሁለተኛ ግብር እየገቡ ይብሉ:: “ሁለተኛ ግብር” ምን እንደሆነ የማያውቅ ይኖር ይሆን? ክቡራኑ ተጋባዦች በልተው ሲወጡ እጃቸውን የጠራረጉበትን ትርፍራፊ እንዲበሉ የሚጋበዙ የሁለተኛ ደረጃ ተጋባዦች ናቸው:: ከዚያ የተረፈ ካለ፥ እደጅ ለተኮለኮሉ ድኾች ይሰጣል:: በዕውቀትና በስልጣና መስክ በስፋት የተሠማሩት የትግራይ ሕዝብ ነፃ አውጪ ግምባር የተወለደባት አገር ልጆች ከሥምሪት ሲመለሱ፥ የሁለተኛው ግብር ሰዴቃው ይነሣል:: ተጋባዦችም በሰላም ይሰናበታሉ፤ ነፃቸውን ይወጡና እደጅ የተኮለኮሉትን ድኾች ቦታ ያጣብባሉ:: አዲስ አበባን የተቈጣጠሩ ማግስት ስፍር ቊጥር የሌላቸውን ሠራተኞች የትም በትነው ሥራቸውን እንደወሰዱባቸው፥ አሁንም ደጋፊያቸው ላልሆነ ሰው የመንግሥት ሥራ እንደማይሰጡ፥ ነፍስ ያለው ሥራ ለማቋቋም ቢፈልግ ባንክ ገንዘብ እንደማያበድረው በሹክሹክታ ሳይሆን በአደባባይ የሚነገርና የሚታይ እውነታ ነው:: እነዚህን መሠሪዎች የመታገል ጊዜው አሁን ነው:: “ከወደቁ በኋላ መገላበጥ ለመላላጥ ነው” ይባላል::

አብሮ ለሚመጣው ጥያቄ የሚሰጠው መልስ መረሳት የለበትም፤ “የትግሬ ወያኔዎች የሚሠሩት ለኢትዮጵያ ሕዝብ ነው” ቢባል እንኳን፥ የኢትዮጵያ ሕዝብ መቼ ሥሩልን አላቸው? በሰው ቤት ገብቶ የሰው ትዳር እንምራ ማለት ነውር ነው፤ ንቀት ነው:: ሕዝቡ በንጉሣዊውና በደርግ አገዛዝ ላይ ያመፀው፥ “የያዛችሁትን ከሕዝብ ያልመነጨ ስልጣን ለሕዝብ ልቀቁ፤ ዘመኑ የዲሞክራሲ ዘመን ነው” ብሎ መሆኑን አልሰሙም ይሆን? እርጉሞች ሆነው ነው እንጂ መስማትስ ሰምተዋል:: ቢሰሙም፥ ያልሰሙ ቢመስሉም፥ የሕዝቡ ጥያቄ አሁንም የዱሮው ነው፤ ስልጣን የሕዝብ ነው:: ዘመኑም የዲሞክራሲ እንጂ፥ የቤተሰብ ስርወ መንግሥታዊና የፈላጭ ቈራጭ አገዛዝስ ዘመናቸው አልፏል::

ዲሞክራሲን ባናየውም፥ ያዩት ሲነግሩን ሰምተን ናፍቆናል።

ዲሞክራሲ ባይታይስ፥ ዜጋ የገዢዎች ተገዢ መሆኑ ቀርቶ፥ ራሱ ገዢ የሚሆንበት ሥርዓት ከሆነ እንዴት አይናፍቅም?

ዲሞክራሲ ባይታይስ፥ እውነተኛ ረትቶ፥ ውሸታም ተረትቶ የሚገባበት ሥርዓት ከሆነ፥ ሥርዓቱ ለእውነተኛ ሰው እንዴት አይናፍቀውም?

ዲሞክራሲ ባይታይስ፥ ዜጋ ሁሉ በሕግ ፊት እኩል የሚሆንበት ሥርዓት ከሆነ፥ እንዴት አይናፍቅም?

ዲሞክራሲ ባይታይስ፥ ፈላጭ ቈራጭ፥ ጨቋኝ ገዢ የሌለበት ሥርዓት ከሆነ፥ እንዴት አይናፍቅም?

ዲሞክራሲ ባይታይም፥ የሚሞቱለት ነው።

ዲሞክራሲ እውነተኛ ነፃነት ዋስ ነው።

ዲሞክራሲ እውነተኛ ነፃነት ፖሊስ ነው።

የሰለጠነው ዓለም የሚተዳደረው በዲሞክራሲ ሥርዓት ነው።

ዲሞክራሲ የኩሩ ሕዝብ ምልክት ነው።

በዲሞክራሲ የማይተዳደር ሕዝብ በረጅም ገመድ የታሰረ ሕዝብ ነው።

ከኋላችን የተወለዱ ሀገሮች ተሟሙተው በዲሞክራሲ ሥርዓት ለመተዳደር ሲችሉ፥ እኛ የጥንቶቹ የምንተዳደረው ዛሬም እንደትናንቱ በፈላጭ ቊራጭ ገዢነት ነው። ከኋላችን ተነሥተው ከቀደሙን ጋር ስንገናኝ የነፃዎችና የእስረኞች፥ የኩሩዎችና አንገታቸውን የደፉ ሰዎች ግንኙነት ይሆናል፤ እነሱ በመሪያቸው ሲኰሩ እኛ በገዢያችን እናፍራለን። እነሱ ታግለው ስላገኙት ነፃነት በኩራት ሲነግሩን፥ እኛ እንቀናባቸዋለን።

**እስከመቸ?**

እስከመቸ? እስከመቸ? እስከመቸ? የኢትዮጵያ ሕዝብ እስከመቸ የሌለ ዲሞክራሲ አለ ሲሉት ዝም ብሎ ይሰማል? እስከመቸ መናቅን ይታገሳል? ከቈረጥን እስከ መጪው ግንቦት ድረስ ብቻ ይሆናል። የኢትዮጵያ ሕዝብ ፈላጭ ቊራጭን ድል ነሥቶ ነፃነቱን ለማወጅ አሁን ለጊዜው ያለው ዕድል የግንቦቱ ምርጫ ነው። ምርጫውን አስታክኮ ሆ ብሎ በአንድነት በኅብረት መነሣት ነው። እንዴት እንደሚደረግ ዝርዝሩን ከጥቂት ቀናት በፊት “ቀኑ ሳይመሽ፥ ብርሃን ሳይሸሽ” በሚል ርእስ ጽፌዋለሁ። የዛሬውም ድርሰቴ ያተኰረው በዚያው ጥሪዬ ላይ እንጂ፥ የወያኔን ጸረ ዲሞክራሲነት በማሳየት የተወሰነ አይደለም።

እንደማየው ከሆነ፥ የተቃዋሚ ቡድኖች በአንድነት ቆመዋል፤ መኢአድ በውይይቱ ቢሳተፍ ኖሮ፥ አንዳንድ ያልተነሡ ነጥቦችን ያክል ነበረ እንጂ፥ ከተነሡት ውስጥ ብዙዎቹ የሚደግፉቸው ናቸው። ወያኔና በዲሞክራሲ እምነት አንድ ቡድን አድርገዋቸዋል ማለት ነው። አዲስ ነበር አይደለም፤ ዱሮም የጋራ ጠላት አባቶቻችንን ያስተባብራቸው ነበር። ምናልባት፥ የተቃዋሚ መሪዎች ወያኔና በዲሞክራሲ እምነት አንድ ወገን እንዳደረጓቸው ልብ አላሉት እንደሆነ፥ ወጣ ብለው የክርክሩን አሰላለፍና የሚሰነዝሩትን የክርክር ሐሳቦች

ይመልከቷቸው። ውይይቱ በፓርቲዎች መካከል ሳይሆን በአንድ ወገን በትግራይ ሕዝብ ነፃ አውጪ ግምባርና በሌላ ወገን በተቃዋሚዎቹ መካከል ነበር። የክርክር ደቂቃዎች ምደባም የሚያንጸባርቀው ይኸንኑ ተወዳዳሪዎቹ ሁለት ቡድኖች ብቻ መሆናቸውን ነው። ወያኔ አንድ ያደረጋቸውን ተቃዋሚዎች ማንም ሊከፋፍላቸው አይገባም። ብዙዎቹ ተቃዋሚዎች፥ በተለየም አቶ ልደቱ አያሌው፥ አቶ ገረሱ ገዳ፥ ፕሮፌሰር መራራ ጉዲና ያቀረቧቸው የክርክር ነጥቦች ማንም ዲሞክራት የሚያምንባቸው ናቸው። ወደኋላ ሄደን ያለፈ ታሪካቸውን እንመርምር ካላልን፥ ተቃዋሚዎቹ አሁን እንዲህ ያለ አንድ ዓይነት ዲሞክራሲያዊ እምነት ካላቸው፥ ለጊዜያዊ ዓላማ በወያኔ ላይ በአንድ ለመሰለፍ ምን ይጎድላቸዋል? ተለያይቶ መቆም የተቃውሞውን ድምፅ መበታተን ነው። ተለያይቶ መቆም ለጠላት አመቺ ዒላማ መሆን ነው። ወያኔ እንኳን ከሰው ከእግዚአብሔርም ጋር ቢወዳደር ምን ጊዜም ምርጫውን በማጭበርበር አሸነፍኩ ማለቱ አይቀርም። የኀብረቱን ቡድንም አሸነፍኩ ሊል ይችላል፤ ግን በአብድነት ሲቆሙ ፓርቲዎቹመም ሕዝቡም በውሸት መሸነፉ እኩል ስለሚሰማው አብረው ሊያምፁበትና ሊጥሉት ይችላሉ።

ሕዝቡ ማድረግ ያለበት ምዝገባውን እያካሄደ ፓርቲዎች በአንድ ረድፍ እንዲሰለፉ ጫና ማክበድ ነው። ሁለቱም ድርጊቶች ያለቅደም ተከተል አብረው የሚሄዱ ናቸው። ወያኔዎቹ ሲያጭበረብሩ፥ "ለምርጫ የሚመዘገበውን ስሙን እየጻፋችሁ ላኩልን" ማለት ጀምረዋል። እንዲህ ያለ ፕሮፓጋንዳ የሚያስተላልፉት፥ "ሕዝቡ ፈሪ ስለሆነ ይበረግግና ከቤቱ ተደብቆ ሳይመዘገብ ይቀራል" የሚል የንቀት እምነት ስላላቸው ነው እንጂ፥ እውነት በሚሊዮን የሚቈጠሩ መራጮችን የመቈጣጠር ችሎታ ኖሯቸው አይደለም። ይኸንን ፕሮፓጋንዳ የኤርትራ ሪፈረንደም ጊዜ አዲስ አበባ ላይ ሠርተውበታል፤ "አገር ወዳድ ተቃዋሚ እንዳይነሣና እንዳያስቸግር እያንዳንዱን ድምፅ ሰጪ ኤርትራዊ ሸጉጥ አስታጥቀነዋል" ብለው አስወርተው እንደነበር አልረሳንም።

ያባቶቻችንን ሀገር ኢትዮጵያን ለማዳን የግንቦት 2002 ዓ.ም. ምርጫ ዕድል ሰጥቶናልና ዕድሉ አያምልጠን። የትግራይ ሕዝብ ነፃ አውጪ ግምባርንና ተለጣፊዎቹን ፓርቲዎች ለመጣል ቈርጠን በኅብረት እንነሣ።

ዓባይ ከምንጭ እንደሚበልጥ ለማየት ያብቃን። ኢትዮጵያን በነፃነቷ ለዘላለም እንድናኖራት አምላኳ ይርዳን።